በስመአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

ባለፈው ክፍል አንድ ላይ አሃድ የሚለውን ቃል ቁርአንን መሰረት አድርገን ማዬታችን ይታወሳል። በዚህ ክፍል ደግሞ ካሉት ሁለት ወሳኝ ቃላት መካከል ዋህድ የሚለውን የምናይ ሲሆን እንደተለመደው ውሳኔውን ለአንባቢ ትተትንና መልስ የሚመልሱ ሙስሊም ወገኖች የፈጣሪ ያሉትን እንጂ የሰው መጽሐፍ እየጠቀሱ እንደማያዝጉን ተስፋ በማድረግ ነው። መልካም ንባብ።

ዋህድ (وَٰحِدٌ) ማለት በቁርአን መሰረት ምን ማለት ነው? ለምን ለምን ጥቅም ላይ ውሏል?

ይህ ቃል አሃድ ከሚለው ቃል በተለየ መልኩ ለተለያዩ ነገሮች ጥቅም ላይ ውሏል ቁርአን ውስጥ። በአጠቃላይ ቃሉ 46 ጊዜ እና ከዛ በላይ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በአንድ አይነት አገባብ ወይም Context ጥቅም ላይ አልዋለም። በአብዛኛው ይህ ቃል ውሑድ የተዋሐዱ ብዙ ሲሆኑ አንድነትን በሆነ መስፈርት ያገኙ የሚልን ትርጉም ሲይዝ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ ድርሻን ለመግለጽ ወይንም ከሆነ ቁጥር ውስጥ የሆነ እጅ ወይም ድርሻን ለማመልከት ሲመጣ አንዴ ደግሞ እያንዳንዳቸውን የሚል ትርጉም ይዞ መጥቷል (24:2 ዋሂዲ ሚንሁም) ብሎታል። እስኪ ለነዚህ አሁን ያልናቸውን ነገሮች ሁሉ ከቁርአን ማስረጃ ከማምጣታችን በፊት Islamic Encyclopedia and dictionary ምን ብለው እንደተረጎሙት እንይ:-

waḥda (A) : oneness; unit, unity, used as a technical term in philosophy and theology (Encyclopaedia of Islam, Second Edition, Glossary and Index of Terms, Edited by: P.J. Bearman, Th. Banquis, C.E. Bowworth, E. van Donzel, W. P. Heinrichs Bowworth. Consulted online on 10 September 2022 http://dx.doi.org/10.1163/1573-3912_ei2glos_SIM_gi_05156).

ዋህድ የሚለውን ቃል እንደሚታየው አንድ መሆን ወይም አንድነት (Unity) ብለውታል እንጂ Singularity ወይም መሰል ትርጉምን አልሰጡትም።

Wahada Allah: the belief in the unity of Allah. To declare Allah to be one, to be monotheist. (Dictionary of Islamic terms by Deeb Alkhubrawi page 524).

ከዚህ በተጨማሪም Arabic Dictionary ተመሳሳይ ትርጉም (አንድነት) Unity ያሉት ሲሆን በተጨማሪም አስረጂ ብለው ያቀረቡት ٱلوحدة العربية Arab unity (የአረብ አንድነት) ያሉት ሲሆን ሌሎች የአረብ አንድነት የሚሉ ተቋሞች በሙሉ አልዋህዱ የሚል ቅጽል መያዛቸውን እንደ ማስረጃ ያቀርባል።

ማንኛውም አረብኛ መዝገበ ቃላት ዋህድ የሚለውን ቃል አንድነት (Unity) አንድ መሆን የሚል ትርጉምን ይዞ የመጣ ሲሆን አሁን ግን የዚህን ቃል ትርጉም መለኮታዊ መጽሐፍ ነው በተባለው በቁርአን መሰረት እስኪ እንይና እውነት ዋህድ ማለት ብዙ ሲሆኑ አንድ የሚል ትርጉም ይሰጣልን የሚለውን እንይ:-

የላሚቱ ምዕራፍ አያ 213 (2:213)

فِيهِ ٱخْتَلَفُوا۟ فِيمَا ٱلنَّاسِ بَيْنَ لِيَحْكُمَ مَعَهُمُ وَأَنزَلَ وَمُنذِرِينَ مُبَشِّرِينَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ٱللَّهُ فَبَعَثَ وَٰحِدَةً أُمَّةً كَانَ ٱلنَّاسُ
مِنَ فِيهِ ٱخْتَلَفُوا۟ لِمَا ءَامَنُوا۟ ٱلَّذِينَ ٱللَّهُ فَهَدَى ۗ بَيْنَهُمْ بَغْيًۢا ٱلْبَيِّنَٰتُ جَآءَتْهُمُ مَا بَعْدِ مِنۢ أُوتُوهُ ٱلَّذِينَ إِلَّا فِيهِ ٱخْتَلَفَ وَمَا ۚ
مُّسْتَقِيمٍ صِرَٰطٍ إِلَىٰ يَشَآءُ مَن يَهْدِى وَٱللَّهُ ۗ بِإِذْنِهِۦ ٱلْحَقِّ

Pickthall

> Mankind were one community, and Allah sent (unto them) prophets as bearers of good tidings and as warners, and revealed therewith the Scripture with the truth that it might judge between mankind concerning that wherein they differed. And only those unto whom (the Scripture) was given differed concerning it, after clear proofs had come unto them, through hatred one of another. And Allah by His Will guided those who believe unto the truth of that concerning which they differed. Allah guideth whom He will unto a straight path.
>
> ሰዎቹ ሁሉ አንድ ሕዝብ ነበሩ፤ (ተለያዩ) ። አላህም ነቢያትን አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች አድርጎ ላከ። ከእነርሱም ጋር መጻሕፍትን በሰዎቹ መካከል በዚያ በርሱ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ በእውነት አወረደ። በእርሱም (በሃይማኖት) ግልጽ አስረጂዎች ከመጡላቸው በኋላ በመካከላቸው ለኾነው ምቀኝነት እነዚያው የተሰጡት እንጂ አልተለያዩበትም። አላህም እነዚያን ያመኑትን ሰዎች ለእዚያ ከእውነት በርሱ ለተለያዩበት በፍቃዱ መራቸው።

ተመልከቱ እዚህ ላይ ሰዎቹ ሁሉ አንድ ሕዝብ ነበሩ ሲል አንድነታቸውን ለመግለጽ የተጠቀመው ቃል ዋሂዳሂ የሚለውን ነው ይህም ዋህድ የሚለው መነሻው ሲሆን ብዙዎቹ አንድ ተብለውበታል። እንቀጥል

የሴቶች ምዕራፍ አያ 102 (4፡102)

> وَلْتَأْتِ وَرَآئِكُمْ مِن فَلْيَكُونُواْ سَجَدُواْ فَإِذَا أَسْلِحَتَهُمْ وَلْيَأْخُذُواْ مَّعَكَ مِّنْهُم طَآئِفَةٌ فَلْتَقُمْ ٱلصَّلَوٰةَ لَهُمُ فَأَقَمْتَ فِيهِمْ وَإِذَا كُنتَ عَنْ أَسْلِحَتِكُمْ وَأَمْتِعَتِكُمْ تَغْفُلُونَ لَوْ كَفَرُواْ ٱلَّذِينَ وَدَّ ۖ وَٰحِدَةً عَلَيْكُم مَّيْلَةً فَيَمِيلُونَ عَلَيْكُم جُنَاحَ وَلَا ۚ فَلْيُصَلُّواْ لَمْ أُخْرَىٰ طَآئِفَةٌ مَعَكَ فَلْيُصَلُّواْ مَعَكَ حِذْرَهُمْ وَلْيَأْخُذُواْ ۗ أَسْلِحَتَكُمْ تَضَعُوٓاْ أَن مَّرْضَىٰٓ كُنتُم أَوْ مَّطَرٍ مِّن أَذًى بِكُمْ كَانَ إِن عَلَيْكُمْ جُنَاحَ وَلَا ۚ حِذْرَكُمْ وَخُذُواْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ أَعَدَّ لِلْكَٰفِرِينَ عَذَابًا مُّهِينًا

Pickthall

> And when thou (O Muhammad) art among them and arrangest (their) worship for them, let only a party of them stand with thee (to worship) and let them take their arms. Then when they have performed their prostrations let them fall to the rear and let another party come that hath not worshipped and let them worship with thee, and let them take their precaution and their arms. Those who disbelieve long for you to neglect your arms and your baggage that they may attack you once for all. It is no sin for you to lay aside your arms, if rain impedeth you or ye are sick. But take your precaution. Lo! Allah prepareth for the disbelievers shameful punishment.

በውስጣቸውም በኾንክና ሶላትን ለእነርሱ ባስገደድካቸው ጊዜ ከእነሱ አንዲት ጭፍራ ካንተ ጋር ትቁም። መሣሪያዎቻቸውንም ይያዙ። በግንባራቸውም በተደፉ ጊዜ ከስተኋላችሁ ይኹኑ። (እነዚህ ይኺዱና) ያልሰገዱትም ሌሎቹ ጭፍሮች ይምጡ። ከአንተም ጋር ይስገዱ። ጥንቃቄያቸውንና መሣሪያዎቻቸውንም ይያዙ። እነዚያ የካዱት ከመሣሪያዎቻችሁና ከጓዞቻችሁ ብትዘነጉና በእናንተ ላይ አንዲትን መዘንበል ቢዘነበሉ ተመኙ። ከዝናብም የኾነ ችግር በእናንተ ቢኖር ወይም ሕመምተኞች ብትኾኑ መሣሪያዎቻችሁን ብታስቀምጡ በናንተ ላይ ኀጢአት የለም። ጥንቃቄያችሁንም ያዙ። አላህ ለከሓዲዎች አዋራጅን ቅጣት አዘጋጀ።

ሙሉ ጭፍራ ከተግባራቸው የተነሳ አንድ ተብለዋል ምክንያቱም ስራቸው ነቢዩን መጠበቅ ስለነበር። አንድነትን ያገኙት በስራቸው ወይም በሚሰሩት ተግብራት እንጂ አካላዊ አንድነትን የሚመለከት አይደለም ምክንያቱም ጭፍራ ተብሏልና።

የዩኑስ ምዕራፍ አያ 19 (10:19)

وَلَوْلَا كَلِمَةٌ سَبَقَتْ مِن رَّبِّكَ لَقُضِىَ بَيْنَهُمْ فِيمَا فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ۞ فَٱخْتَلَفُوا۟ وُحِدَةً أُمَّةً إِلَّآ ٱلنَّاسُ وَمَا كَانَ

Pickthall

Mankind were but one community; then they differed; and had it not been for a word that had already gone forth from thy Lord it had been judged between them in respect of that wherein they differ.

ሰዎችም አንድ ሕዝብ እንጂ ሌላ አልነበሩም። ተለያዩም። ከጌታህ ያለፈች ቃልም ባልነበረች ኖሮ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው በእርግጥ (በቶሎ) በተፈረደ ነበር።

ብዙ ሰዎች ሕዝብ ሆነው ሳለ አንድ ተብለዋል።

የሁድ ምዕራፍ አያ 118 (11:118) ፣ የመመካከር ምዕራፍ አያ 8 (42:8)

مُخْتَلِفِينَ يَزَالُونَ وَلَا ۝ وُحِدَةً أُمَّةً ٱلنَّاسَ لَجَعَلَ رَبُّكَ شَآءَ وَلَوْ

Pickthall

And if thy Lord had willed, He verily would have made mankind one nation, yet they cease not differing,

ጌታህም በሻ ኖሮ ሰዎችን ሁሉ አንድ ሕዝብ ባደረጋቸው ነበር። የተለያዩም ከመሆን አይወገዱም።

42:8

وَلَا نَصِيرٍ وَلِيٍّ مِّن لَهُم مَا وَٱلظَّٰلِمُونَ ۚ رَحْمَتِهِۦ فِى يَشَآءُ مَن يُدْخِلُ وَلَٰكِن وُحِدَةً أُمَّةً لَجَعَلَهُمْ ٱللَّهُ وَلَوْ شَآءَ

Pickthall

Had Allah willed, He could have made them one community, but Allah bringeth whom He will into His mercy. And the wrong-doers have no friend nor helper.

አላህም በሻ ኖሮ (ባንድ ሃይማኖት ላይ) አንድ ሕዝብ ባደረጋቸው ነበር፡፡ ግን የሚሻውን ሰው በእዝነቱ ውስጥ ያስገባል፡፡ በዳዮችም ለእነርሱ ወዳጅና ረዳት ምንም የላቸውም፡፡

አንድ ሕዝብ ባደረጋቸው ነበር ሲል የሚጠቀመውን ቃል አስተውሉ ዋሂዳሃ ነው። ብዙ ሰዎች አንድ ተብለዋል። አንድ የሚሆኑበትም በአካል ሳይሆን በሚከተሉት፣ በሚያመልኩት አምላክ ነው። አንድ ሲል አካላዊ አንድነትን አያሳይም።

የአረጋጋጪቱ ምዕራፍ አያ 14 (69፡14)

وَٰحِدَةً دَكَّةً فَدُكَّتَا وَٱلْجِبَالُ ٱلْأَرْضُ وَحُمِلَتِ

Pickthall

And the earth with the mountains shall be lifted up and crushed with one crash,

ምድርና ጋራዎችም (ከስፍራቸው) በተነሱና አንዲትን መሰባበር በተሰባበሩ ጊዜ፡፡

ምንም እንኳን ጋራዎች በዙ ቢሆኑም መሰበራቸው ግን አንዲት መሰበር ተብሎ ተነግሯል።

የአውጪዎች ምዕራፍ አያ 13 (79፡13)፣ የተሰላፊዎች ምዕራፍ አያ 19 (37፡19)፣ የያሲን ምዕራፍ(36፡ 49,53)

ከላይ የዘረዘርናቸው አያዎች በሙሉ የፍጥረትን ጩኸት አንድ ወይም ዋሃዳሁ ፣ዋሂዳሃ ብለውታል ለናሙና ያክል 37፡19 ይኸው፡-

يَنظُرُونَ هُمْ فَإِذَا وَٰحِدَةٌ زَجْرَةٌ هِيَ فَإِنَّمَا

Pickthall

There is but one Shout, and lo! They behold,

እርሷም አንዲት ጩኸት ብቻ ናት፡፡ እነርሱም ወዲያውኑ (ምን እንደሚፈጸምባቸው) ያያሉ፡፡

የህዝቡ ሁሉ ጩኸት አንድ ተብሏል። ሕዝብ የሚለው አካላዊ ብዙነታቸውን የሚያሳይ ሲሆን ጩኸታቸው ግን አንዲት ተብሏል የዛ ሁሉ ሕዝብ።

እስካሁን ከቁርአኑ እየነቀስን እያወጣን ያየናቸው አያዎች እንደሚያሳዩት ዋህድ የሚለው ቃል ልዩ፣ ብቸኛ፣ የሚመስለው የሌለ ወዘተ የሚሉ ነገሮችን ሳይሆን ብዙ ሲሆኑ አንድ ተብለው ለተጠሩ ነገሮች ሰዎች ወዘተርፈ ጥቅም ላይ ውሎ እናገኘዋለን።

አሁን ደሞ እስኪ የሰዉ ሁሉ ነፍስ አንዲት ተብላ እንደተገለጠች እንይ፡-

የሉቅማን ምዕራፍ አያ 28 (31፡28)

بَصِيرٌ سَمِيعٌۢ ٱللَّهَ إِنَّ ۗ وَٰحِدَةٍ كَنَفْسٍ إِلَّا بَعْثُكُمْ وَلَا خَلْقُكُمْ مَّا


Pickthall

> Your creation and your raising (from the dead) are only as (the creation and the raising of) a single soul. Lo! Allah is Hearer, Knower.
>
> እናንተን መፍጠርና እናንተን መቀስቀስ እንደ አንዲት ነፍስ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ አላህ ሰሚ ተመልካች ነውና፡፡

በእንግሊዝኛውም ሆነ በአማርኛው እንደሚታየው ከነፍሲ ዋሂዳቲ ከአንዲት ነፍስ ወይም Single soul ብሎ የሰውን ሁሉ ነፍስ አንዲት ብሏት ይገኛል። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ (ከአንዲት ነፍስ የሰውን ነፍስ ሁሉ ማስገኘት) 6፡98 እና 7፡189 ላይ ላለው አንዲት ነፍስ ለሚለው አስረጂ ሲሆን ይሄ መቼም የቁጥር አንድነት አለመሆኑ ግልጽ ነው። አንዲት ነፍስ ያሰኛት ባህርይዋ ፍጡር መሆኗ (ባህርያዊ ተዋሕዶ ባህርያዊ አንድነት) ወዘተ እንጂ በቁጥር ደረጃ (Numerically one፣ singularity) አንድ ማለት አይደለም። ነፍስ ከምንነቷ ተነስትው አንዲት ስትባል ይሄ አንድነቷን ማጤንና የቁጥር አንድነት አለመሆኑን አንባቢ ያስተውል። ስለዚህ አላህ አንድ ነው ሲባል አንድ ምን? የሚለው ጥያቄ ክርስቲያናዊ ብቻም ሳይሆን እስላማዊ ጥያቄ ሆኖ እናገኘዋለን። “አንድ” በምንነት ደረጃ ከሆነ ከክርስትናው አስትምህሮ የሚሄድና ይሄ አንድነት ማንነታዊ ብዝሃነትን የሚቀበል በመሆኑ ብትክክልም መጽሐፋዊ ይሆናል እምነታቸው። ኢይይ ይሄ አንድነት አካላዊ ነጠላ ማንነት ነው ከተባለ ደግሞ ያንን የሚያመላክት አስረጂ ማቅረብ ግድ ይሆናል። ነጠላ አካላዊ ማንነት አለው የሚል ቁርአናዊ ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም። ከዚህ ቀጥልን እንደምናዬው ይህ ዋህድ የሚል ቃል ለአላህ ተቀጽሎ የመጣባቸው አያዎች ላይ ከሱ ውጪ ሌሎች አካላትንም እናገኛልንና። ምናልባት አሁንም ማስረጃዎችን ያበዛነው አንድ ቦታ ላይ ነው ሌላ የለም ምናምን ማለቃቀሻ እንዳይበዛ በማሰብ ነው። አንዲት አያም ብትሆን የአላህ ባህርይ ነው ከተባለው ቁርአን ውስጥ ማግኘት ለማስረጃ ሚሆን ቀላል ነገር አይደለም አይደለም ይሄ ሁሉ ተዘርዝሮ።

ከእነዚህ በተጨማሪም ይህ ዋህድ የሚል ቃል እያንዳንዱ Each and everyone የሚል ትርጉም እና ከሆነ ቡድን ውስጥ አንዱን ነጥሎ ለማውጣት ተጠቅመውበት እናገኛለን 38፡23 ከ99 በጎች አንዲት አለቺኝ የሚል ሲኖር 24:2 ላይ ደግሞ እያንዳንዱ የሚል ትርጉምን ይዞ መጥቷል።

ይህ ቃል በተለያዩ ሱራዎች ለአላህ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን “አንድ” ተብሎ ተተርጉሞና ያንኑም ትርጉም ይዞ እናገኘዋለን። ሁሉም ቦታ ለማለት በሚያስችል መልኩ ይህ ዋህድ የሚለው ቃል ለአምላክ ተቀጽሎ ሲመጣ አላህ የሚለውን ሳይሆን ኢላሁኩም፣ ኢላሁና፣ ኢላህ ወዘተ የተሰኙ አላህ የሚለውን ስም ያላካተቱ ሆነው መጥተዋል። አላህ የሚለውን አካትተው ሲመጡ ደግሞ ብቻውን ሳይሆን ሊሎች አካላትን ለምሳሌ ብዙ ጣዖታትንና ኢሳ ኢብነ መርየምን ጨምሮ ነው የመጣው። ይህ ማለትም ቃሉ ነጠላ ማንነት ማለት ነው የሚለውን ትርጉም ከላይ ስናይ እንደመጣነው የሚያፈርስና አላህ ውሑድ አንድ ወይም Compound unity with many other gods አለው የሚል ፍንጭ የሚሰጥ ይሆናል። ከዚህ በመቀጠል በመጀመሪያ ነቢዩ መሐመድ ወደ የመን የላከውን መልእክት እና እነሱ ያመኑትን ትምህርት መሰረት አድርገን የዚህን ቃል ትርጉም የበለጠ እንሰነጥቀዋለን። Sahih Bukhari 7371 ይመልከቱ



Collection	Sahih Bukhari
Dar-us-Salam reference	Hadith 7372
In-book reference	Book 97, Hadith 2
USC-MSA web (English) reference	Volume 9, Book 93, Hadith 469

Narrated Ibn `Abbas:
When the Prophet (ﷺ) sent Mu`adh to Yemen, he said to him, "You are going to a nation from the people of the Scripture, so let the first thing to which you will invite them, be the Tauhid of Allah. If they learn that, tell them that Allah has enjoined on them, five prayers to be offered in one day and one night. And if they pray, tell them that Allah has enjoined on them Zakat of their properties and it is to be taken from the rich among them and given to the poor. And if they agree to that, then take from them Zakat but avoid the best property of the people."

وَحَدَّثَنِي عَبْدُ اللَّهِ بْنُ أَبِي الأَسْوَدِ، حَدَّثَنَا الْفَضْلُ بْنُ الْعَلاَءِ، حَدَّثَنَا إِسْمَاعِيلُ بْنُ أُمَيَّةَ، عَنْ يَحْيَى بْنِ عَبْدِ اللَّهِ بْنِ مُحَمَّدِ بْنِ صَيْفِيٍّ، أَنَّهُ سَمِعَ أَبَا مَعْبَدٍ، مَوْلَى ابْنِ عَبَّاسٍ يَقُولُ سَمِعْتُ ابْنَ عَبَّاسٍ، يَقُولُ لَمَّا بَعَثَ النَّبِيُّ صلى الله عليه وسلم مُعَاذًا نَحْوَ الْيَمَنِ قَالَ لَهُ
" إِنَّكَ تَقْدَمُ عَلَى قَوْمٍ مِنْ أَهْلِ الْكِتَابِ فَلْيَكُنْ أَوَّلَ مَا تَدْعُوهُمْ إِلَى أَنْ يُوَحِّدُوا اللَّهَ تَعَالَى فَإِذَا عَرَفُوا ذَلِكَ فَأَخْبِرْهُمْ أَنَّ اللَّهَ فَرَضَ عَلَيْهِمْ خَمْسَ صَلَوَاتٍ فِي يَوْمِهِمْ وَلَيْلَتِهِمْ، فَإِذَا صَلُّوا فَأَخْبِرْهُمْ أَنَّ اللَّهَ افْتَرَضَ عَلَيْهِمْ زَكَاةً فِي أَمْوَالِهِمْ تُؤْخَذُ مِنْ غَنِيِّهِمْ فَتُرَدُّ عَلَى فَقِيرِهِمْ، فَإِذَا أَقَرُّوا بِذَلِكَ فَخُذْ مِنْهُمْ وَتَوَقَّ كَرَائِمَ أَمْوَالِ النَّاسِ "

ከላይ ያስቀመጥነው ሳሂህ ሃዲስ እንደሚነግረን መሐመድ ከሂጅራ 9 ዓመት በኋላ ጣዖት ያመልካሉ ወደተባሉት የመናውያን የላከው መልእክት ሲሆን “ኢና ዩአሂዱ አላህ” አላህን አንድ ያደርጉ ዘንድ ብሎ የላከው መልእክት ውስጥ ይህን ዋህድ ከሚለው ስርው የሚመዝዝ ቃል የተጠቀመ ሲሆን ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው “አላህን አንድ ያደርጉ ዘንድ” የሚል ቀጥተኛ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ነው። ይህ መልእክት ብቻ ብዙ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ያስገድደናል። በመጀመሪያ ደረጃ ጣዖት አምላኪያን አላህን አንድ አድርጉ የሚባሉት ስንት አድርገውት ኖረው ነው? ምናልባት ሙሽሪክ ስለነበሩ ሌሎች ጣዖታትን ተዋቸው አላህን በብቸኝነት ተገዙት የሚል ቢሆን ኖሮ መልእክቱ ሌሎችን ጣዖታት ተዋቸው ወዘተ በማለት መልእክት ይልክ ነበር እንጂ አላህን በተመለከተ አንድ አድርጉ ብሎ አይልክላቸውም ነበር። ከዚህ መልእክት የምንረዳው መሐመድ እየነገራቸው ያለው ሰልማያውቁት ሰለትክክለኛው አምላክ ሳይሆን Already ስለሚያውቁት ስለሚያመልኩት ግን አንድ አድርገው በማይገዙት ጣዖት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም ወደ ጣዖት አምላኪ ሕዝቦች ሄዶ አላህን የምትገዙትን አንድ አድርጉ ማለት አላህ ከሚገዟቸው ውስጥ አንዱ (አሃደን) ነበር እንጂ ያልነበረ እውነተኛ ጌታ ስብከት አይሆንም። ምናልባት ወደ ዋናው ርዕሳችን እንመለስና የዚህን ዋህድ የሚል ቃል ጥቅም በቁርአኑ እንይ፡-

ኢላሁ፣ ኢላሁኩም፣ ኢላህ ወዘተ ከተባለ በኋላ ዋህድ(وَٰحِدٌ) የተባለባቸው አንቀጾች ብዙ ሲሆኑ የሚከተሉትን ለማሳያነት አቅርበናል 2:163, 5:73, 6:19, 16:22, 21:108, 41:6, 22:34። ለማሳያነት እነዚህን አቀረብን እንጂ ከዚህም በላይ አሉ አማላካችሁ አንድ ነው የተባለበት (ተናጋሪው አላህ ነው ተብሎ ይታመናል ሙሉ ቁርአን ውስጥ፣ ነገር ገን ነኝ ለምን እንደማይልና ይህ አገላለጽ የጂብሪል ላለመሆኑ ምን ማስረጃ እንዳለ አላውቅም፣ ምክንያቱም ሌላ አካል ስለሌላ አካል እየገለጸ እንጂ ያው አካል ስለራሱ እያወራ አለመሆኑንና ቁርአኑ በጂብሪል አማካኝነት ውረደለት መባሉንና መሐመድ ቀጥታ ከአላህ አለመስማቱ ሲታሰብ ይህ አገላለጽ የጂብሪል ላለመሆኑ ከጭፍን እምነት ባሻገር ምን ማስረጃ እንዳለው አስቡበት)።

እስካሁን እንዳየነው አላህ አሃድ(አንዱ) አንድ ጊዜ ብቻ እና ዋህድ(አንድነት) በብዙ ቦታዎች ከተባለ አላህን የበለጠ የሚገልጠው አንዱ የሚለው አሃድ ወይስ አንድነትን (ውሑድ ምንነትን) የሚገልጸው ዋህድ? ሁለቱም እንዳይባል ሁለቱም አንድ አይነት ትርጉም የላቸውም! አላህን የበለጠ የሚገልጸው አሃድ ወይስ ዋህድ? አሃዱ የተባለስ ከምን? ከነማን መካከል ነው

አንዱ የተባለው? ዋህድ የተባለስ ከምን ከነማን ጋር ነው አንድነትን ያገኘው? ውይስ አሃዱ ሚን ዋህዱን ነው? ወይስ ምን የሚሉ ነገሮችን ማጤንና ማስተዋል ይገባናል።

ምናልባት ዋሕድ የሚለው ለአላህ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ ነው የሚል አይጠፋምና አላህ ከማንና ከነማን ጋር ውሑድ አንድ እንደተባለ ቁርአኑን መሰረት አድርገን እንይ፡-

29:46

وَإِلَٰهُنَا إِلَٰهُكُمْ وَٰحِدٌ وَنَحْنُ لَهُۥ مُسْلِمُونَ وَإِلَيْكُمْ وَأُنزِلَ إِلَيْنَا أُنزِلَ بِٱلَّذِى ءَامَنَّا وَقُولُوٓا۟ ۖ مِنْهُمْ ظَلَمُوا۟ ٱلَّذِينَ إِلَّا أَحْسَنُ هِىَ بِٱلَّتِى إِلَّا ٱلْكِتَٰبِ أَهْلَ وَلَا تُجَٰدِلُوٓا۟

Pickthall

And argue not with the People of the Scripture unless it be in (a way) that is better, save with such of them as do wrong; and say: We believe in that which hath been revealed unto us and revealed unto you; our Allah and your Allah is One, and unto Him we surrender.

የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፡፡ ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡፡ በሉም «በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን፡፡ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፡፡ እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን፡፡»

ይህ አንቀጽ ብዙ ቁምነገሮች ሊወጣው የሚችል ቢሆንም ለጊዜው “ወኢላሁና ወኢላሁኩም ዋሂዱ’ አምላካችሁ አምላካችን አንድ ነው የተባለበትን ክፍል ብቻ እንድታዩልኝ እፈልጋለሁ። የመጽሐፉ ሰዎች ኢሳ አልመሲሕን ጌታ አምላክ አድርገው ያዙ ብሎ የከሰሰው አላህ እዚህ ላይ ከዚያው አምላካቸው ነው ብሎ ምስክርነት ከሰጠው አካል ጋር አንድ ነን እያለ ይገኛል። ከዚህ የምንረዳው ቁምነገር አላህ ከኢሳ አልመሲሕ ጋር (የክርስቲያኖች ክርስቶስ አይደለም የመሐመድ ፈጠራ እንጂ) አንድነትን እያወጀ ታገኙታላችሁ በመሆኑም ይህ ዋህድ የሚለው ለአላህ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ ሳይሆን ከኢሳ ጋርም አላህ ያለውን አንድነት ለመግለጽ ተጠቅሞበታል። ኢሳን መሳደብ ማንን መሳደብ እንደሆነ ሙስሊም አስተውል በዚሁ። ምናልባት አላህ ከኢሳ ጋር ያለውን አንድነት የገለጸበት አያ ይህ ብቻ አይደለም። 9:31 ላይም የገለጸው ሲሆን ለዚህም ምናልባል ሌላ ጽሑ ቢያስፈልገውም እንየው፡-

9:31

ۚ هُوَ إِلَٰهَ لَآ ۖ وَٰحِدًا إِلَٰهًا لِيَعْبُدُوٓا۟ إِلَّآ أُمِرُوٓا۟ وَمَآ مَرْيَمَ ٱبْنَ وَٱلْمَسِيحَ ٱللَّهِ دُونِ مِّن أَرْبَابًا وَرُهْبَٰنَهُمْ أَحْبَارَهُمْ ٱتَّخَذُوٓا۟ عَمَّا يُشْرِكُونَ سُبْحَٰنَهُۥ

Arberry

They have taken their rabbis and their monks as lords apart from God, and the Messiah, Mary's son -- and they were commanded to serve but One God; there is no god but He; glory be to Him, above that they associate –

ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲኾኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን ከአላህና ከመርየምን ልጅ አልመሲሕ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፡፡ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው፡፡

ምናልባት የአማርኛው ቁርአን አረብኛውን በድሎ “ሚን ዱኒ ላሂ ወልመሲሕ ኢብነ መርየም” የሚለውን አላህና አልመሲሕን በ”ወው” ሃርፉ ያያየዘውን ነጥሎ ስለወሰደው ከእንግሊዝኛው ላይ በተመለከተው ትክክለኛ ትርጉምን በሚወክል ወስጀዋለሁ። ምናልባትም ቁርአን ወደ አማርኛ ሲመጣ ከተጣመሙ አያዎች አንዱ ይህ ስለሆነ ተገቢውን ማስተካከያ ከእንግሊዝኛው ጋር በማስተያየት ስላስቀመጥኩት አማርኛውን ቁርአን ብቻ የምታነቡ ሰዎች ግራ እንዳትጋቡ ትክክለኛው አገባብ ይሔ ነው ማለት እወዳለሁ። እዚህ ላይም እንደምንመለከተው አላህና አልመሲሕ አንድ አምላክ ተብለው እናገኛለን። ምናልባት ይሄ የማይዋጥላቸው ብዙ የዋሃን ሙስሊማን ወሙስሊማት ይኖራሉና አላህ አይደለም የተከበረ ከተባለው ከኢሳ ጋር ይቅርና ከጣዖታትም ጋር አንድ መባሉን እንመልከት።

39:5

عُجَابٌ لَشَىْءٌ هَٰذَا إِنَّ ۖ وَٰحِدًا إِلَٰهًا ٱلْءَالِهَةَ أَجَعَلَ

Arberry

What, has he made the gods One God? This is indeed a marvellous thing.'

«አማልክቶቹን አንድ አምላክ አደረጋቸውን? ይህ አስደናቂ ነገር ነው»

የዚህን አስባቡል ነዙል ብትመለከቱ ሌሎች አማልክት የተባሉት ጣዖታት ሲሆኑ አንድ አምላክ የተባለው ደሞ አላህ ነው። በአስባቡ የምናገኛቸው ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው መሐመድ ገና ስብከቱን ሲጀምር ያመጹ ቀረይሾች ያቀረቡበት ክስ እንደነበርና ያም ክስ አማልክትን ሁሉ አንድ አደረጋቸው በማለት ያሙት መሆኑን እንረዳለን። አንድ አደረጋቸው ያሉትም የሊጥ አምላክ፣ የሰብል አምላክ፣ የጦርነት አምላክ፣ የማሕጸን አምላክ፣ የጽንስ አምላክ ወዘተ እያሉ የሚገዟቸው ብዙ ጥዖታትን እንደሆነና መሐመድ አንድ አደረጋቸው ያሉት እነዚህን ሁሉ ጠቅልሎ አንድ ብቻ ይበቃችኋል እንዴት ይለናል የሚል ክስ ነበር ያቀረቡበት። እንግዲህ ከሰበቡል ነዙሉ የምንረዳው አንድ አደረጋቸው የተባለው አላህ መሆኑንና አንድነቱ ደግሞ ከነሜን ጋር መሆኑን አንባቢ ያስተውል (ከጣዖታቱ ጋር ነው)። ምናልባት በዝቶ እንዳይዘነጋ የባለፈውን ክፍልና የዚህን ክፍል መደምደሚያ ከሰጠን በኋላ በቀጣይ ክፍል ክርስቲያኖችስ አምላክ ሶስት አካል የሚለውን ትምህርት ከየት አመጡት? መጽሐፍ ቅዱስ ከአንድ አካል በላይ ያለውን እግዚአብሔር ይሰብካል ወይ? ይህ እምነትስ መጽሐፍትን መሰረት ያደረገ ወይስ የሊቃውንት ፈጠራ? ተውሒድ የሚለው ቃልስ ለአላህ ወይስ ለስላሴ የሚመጥነውና የሚገባው? የሚለውን እንመለከታለን እስከዛ ደካማ ወንድማችሁን በጸሎታችሁ አስቡኝ እግዚአብሔር ዓይነ-ልቡናዬን ከፍቶ ያሳየኝና ቅዱስ መንፈሱን እንዳላስመርር እንዲረዳኝ ምሕረትን ለምኑልኝ እላለሁ።

መደምደሚያ፥-

1. አሃድ (أَحَدٌ) እና ዋህድ (وَٰحِدً) አንድ አይነት ቢምስሉም የተለያዩ ቃላት ናቸው
2. ዋህድ አንድነት (Unity) ማለት ሲሆን አሃድ ግን ከሆነ ቡድን (group) መካከል አንዱ ማለት ነው
3. አላህ አሃድም ዋህድም ተብሏል። የቱ ነው? አላህ በዓረብ ከነበሩ ጣዖታት ጋርም መጥቷል አሃድም ተብሏል አንዱ የተባለው ከነሜን መካከል ነው? አላህን የተሻለ የሚገልጸውስ ዋህድ ወይስ አሃድ? አላህ ዋህድ ይሁን አሃድ ቁርአኑን መሰረት በማድረግ አይታወቅም

4. አላህ ነጠላ ብቸኛ Singular in his essence and person አካላዊና ባሕርያዊ አንድነት ያለው ነው የሚል አንድም ማስረጃ የለም። በነሱው ትርጉም እንኳን ብንሄድ ቁርአኑ በደፈናው አንድ ነው ይላል እንጂ አንድ ምን? ምን አይነት አንድነት ነው ያለው? ለሚለው ምንም አይነት መልስ አይሰጥም።